ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት

**Global Alliance for the Rights of Ethiopians (GARE)**

**PO Box 1836, Rancho Cordova, CA 95741 Telephone: (877)746 -4384**
**www.GlobalAlliancefortheRightsofEthiopians.org**
**info@defendethiopians.org**

**All Lives Have Equal Value**

**November 14, 2017**

ለተከበራችሁ: ከበርሊን የኢትዮጵያውያን ማህበን :

ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት (Global Alliance for the Rights of Ethiopians) ከተመሰረተበት ጥቅምት ወር ፪ ፲ ፻ ፮ ዓ.ም. (November 2013) ጀምሮ በስደት ለሚገኙ ወገኖቹ ያልተቆጠበ ድጋፍ አድርጓል። ይህ ድጋፍ ስኬታማ ሊሆን የቻለው በመላው ዓለም በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ቅንነትና ድጋፍ ነው። የእነዚህን ኢትዮጵያውያን ድጋፍ አስተባብሮና አቀናጅቶ ተአማኒነት ባለው አለም አቀፍ (International) የግብረ ሠናይ ድርጅት አማካይነት ዕርዳታውን በቀጥታ ለተጎዱ ወገኖቻችን በማድረስ ውጤቱንም በይፋ ለሕዝብ በማሳይት ድርጅታችን ተደማጭነትንና ታማኝነትን ለማግኘት የቻልነው በእናንተ ድጋፍ አማካይነት ነው።

በዚህ አጋጣሚ የዜግነታችሁን ግዴታ በመወጣት በአሁኑ ግዜ ባገራችን ውስጥ እየተካሄደ ባለው ግድያ እና ህዝባችን ከሚኖሩበት ለሚፈናቀሉ ወገኖቻችን እንዲደርስ የላካችሁልንን **$ $4,093.20**. የአሜሪካ ዶላር የደረሰን መሆኑን ከታላቅ ምስጋና ጋር እያረጋገጥን እርዳታችሁ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ከሚልኩት ጋር ተደምሮ በቀጥታ ለተጎዱት ወገኖቻችን እንዲደርስ የምናደርግ መሆኑን ልናረጋግጥ እንወዳለን።

የችግሩ መጠን እያደገ በመሄዱ ለወደፊቱም ያልተቋረጠ ድጋፋችሁን እንድትቀጥሉ በተጎዱት ወገኖቻችን ስም አጥብቀን እናሳስባለን።

ከታላቅ አክብሮት ጋር

ታማኝ በየነ ሊቀመንበር

ዓለም አቀፍ ትብብር ለኢትዮጵያውያን መብት

**Global Alliance for the Rights of Ethiopians (GARE)**

**PO Box 1836, Rancho Cordova, CA 95741 Telephone: (877)746 -4384**

**www.GlobalAlliancefortheRightsofEthiopians.org**

**info@defendethiopians.org**

**All Lives Have Equal Value**